


## COVID-19 ለታክሲ፣ ለኡበር ሾፌሮችና ለሌሎች በግል ሥራ ለሚተዳደሩ

## ተደጋጋሚ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

**Original source for most information below**:
https://cupe.ca/canada-emergency-response-benefit-qa

**ጥያቄ፡** እኔ የታክሲ/የኡበር/የሊፍት ሾፌር ወይንም በ፤ግል ሥራ የምተዳደር ነኝ በኮቪድ ምክንያት መሥራት አልቻልኩም። ለቅጥር ዋስትና ክፍል (EI ) ክፍያ ለመጠየቅ ማመልከት አልችልም ለሌላ መንግሥታዊ ጥቅማ ጥቅሞች ለማመልከት ብቁ ነኝ?

**መልስ ፦** አዎ  በኮቪድ-19 ምክንያት ምንም ገቢ የሌላቸው፣ ወይንም ገቢ የቀነሰባቸው ሆኖም ግን ከሥራ ያልተሰናበቱ  ለአዲሱ የካናዳ አስቸኳይ እገዛ ፕሮግራም (CERB) ተካተዋል። ይህም ማለት የኮንትራት ሠራተኞች፣ ምትክ ሠራተኞች፣ እና በግል ሥራ የሚተዳደሩ (ታክሲ/ኡበር/ሊፍት ሾፌሮችን) ጭምር በዚህ ፕሮግራም ይጠቃለላሉ።

**ጥያቄ፡** ታክሲ/ኡበር/ሊፍት ሾፌሮች እና በግል ስራ ተዳዳሪዎች ለአስቸኳይ እገዛ ፕሮግራሙ CERB?) ወዲያውኑ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ?

**መልስ፡** የለም ሁሉም ተጠቃሚ አይደሉም። የለም ሁሉም ተጠቃሚ አይደሉም። በዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን አመልካቾች በ2019 ወይም ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ ባለፉት 12 ወራት $ 5000 ገቢ የነበራቸው ሊሆኑ ይገባል። ይህ ገቢ የቅጥር ገቢ፣ የግል መተዳደሪያ ሥራ ገቢ፣ ወይንም የወሊድ ዕረፍት ገቢ፣ ወይንም የወላጅ ከሥራ በማረፍ የሚገኝ ጥቅማ ጥቅምም ሊሆን ይችላል።

**ጥያቄ** የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ  እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

**መልስ፡** የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB) ማመልከቻ ቅፅ በኦንላይን April 6, 2020. ታገኛላችሁ። ድረገፁ ገና አልተገለፀም ድረገፁ በተገለፀ ጊዜ በኛ ድረገፅ  https://ethioerisupport.webnode.com/  ላይ መረጃውን እናወጣለን።

**ጥያቄ ፡** ከካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ምን ያህል ገንዘብ አገኛለሁ? መቼ ነው የማገኘው?

**መልስ፡** የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB) የሚከፍለው ከማርች 15 ጀምሮ ለአራት ወራት የሚከፈል በወር $2,000 ይሆናል። ማመልከቻውን ባሥገቡ በ10 ቀናት ውስጥ ክፍያውን ያገኛሉ። ይህም ማለት ቀጥታ ወደ ባንክ የሚዘዋወር ከሆነ በአፕሪል 16 2020 በፖስታ የሚላክ ቼክ ከሆነ ደግሞ ምናልባት ጥቂት ቀን ሊዘገይ ይችላል።

**ጥያቄ ፡** ለቅጥር ዋስትና (EI) አመልክቼ ከሆነስ? እንደገና ለካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB) ማመልከት ይኖርብኛል?

**መልስ።** የለም ለቅጥር ዋስትና ክፍል (EI) , አመልክተው ከሆነ ማመልከቻዎ ቀጥታ ወደዛ ስለሚዘዋወርና ለ16 ሳምንታት በዛው ማመልከቻ ስለሚከፈልዎት የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB) ማመልከት አይኖርብዎትም።

**ጥያቄ፡** እስካሁን ድረስ ለቅጥር ዋስትና ክፍል (EI) ያላመለከትኩ ከሆነ ለቅጥር ዋስትና ክፍል(EI) ላመልከት ወይንስ የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ማመልከቻን ልጠብቅ?

**መልስ፡** ይህ ጥያቄ መልሱ እስካሁን ግልፅ አይደለም። ለጥንቃቄ ሲባል ምናልባት ለቅጥር ዋስትና ክፍል ማመልከት ይችሉ ይሆናል። አለበለዛ ግን እስከl April 6 ጠብቀው የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB) ማመልከት ይችላሉ።

**ማሳሰቢያ:** አፕሪል 6 ማመልከቻው ሲለቀቅ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት ሁሉ በተመሳሳይ ጊዜ ስለሚጠቀሙበት የቴክኒክ ችግር ሊያጋጥም ስለሚችል ከወዲሁ ይዘጋጁ

**ጥያቄ :** የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB) ተጠቅሜ ከጨረስኩ በኋላ ሕመም ላይ ብሆን፣ ወይንም ሥራ አጥ ብሆንስ?

**መልስr:** በቂ የቅጥር ዋስትና ክፍል ክፍያ ያለዎት ከሆነ ከአራት ወራት በኋላ የካናዳ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (CERB). ሲያበቃ የቅጥር ዋስትና ክፍል ክፍያዎን መውሰድ ይችላሉ።